# የጤናና ደህንነት መዝገብ አያያዝ

**መዝገቡን መያዝ ያለብዎ ጊዜ ርዝመት እንደ መዝገቡ አይነት ላይ ይመሰረታል።**

ለምሳሌ፡ የኦኤስኤችኤ 300 መዝገቦች ቢያንስ ለአምስት ዓመታት መያዝ እና መቀመጥ አለባቸው።





## መያዝ ያለባቸው የጤናና ደህንነት መዝገቦች፡

- የአደጋ መከላከል ፕሮግራም (የጽሁፍ)
- የሰራተኛ የህክምናና ተጋላጭነት መዝገቦች
- የፌደራል ኦኤስኤችኤ 300 የጉዳት/ ህመም መዝገቦች
- ከልዩ የስራ ቦታ ላይ አደጋዎች ጋር ተያያዥ መዝገቦች
- አደገኛ መድሀኒቶችን ጨምሮ የአደገኛ ኬሚካሎች የደህንነት ዳታ ቅጾች
- የደህንነት ስብሰባ መዝገቦች (ቀናት፣ የስብሰባ ርዕሰ ጉዳዮች፣ እና የተሳተፉ ሰራተኞች)
- የደህንነት ስልጠና መዝገቦች (የስልጠና ርሰ ጉዳዮች፣ ቀናት እና የተሳተፉ ሰራተኞች)

በደም ንክኪ የሚተላለፍ በሽታ ተጋላጭነት የህክምና መዝገቦች በሚስጥር መያዝ እና ለስራ ቅጥር ዘመን ሲደመር 30 ዓመታት መያዝ አለባቸው።

## በደም ንክኪ የሚተላለፍ በሽታ ተጋላጭነት የህክምና መዝገቦች

- የሄፒታይተስ ቢ ክትባት እና የድህረ ተጋላጭነት ግምገማዎች
- የጤና እንክብካቤ አቅራቢ የጽሁፍ አስተያየቶች
- እንደ አስፈላጊነቱ በጤና እንክብካቤ አቅራቢ የተሰጠ መረጃ

